# በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ሚኒስቴር

# የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት መመሪያ

# ቁጥር 529/2013

ጥቅምት 2009 ዓ/ም

<u>አዲስ አበባ</u>

# የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት መመሪያ ቁጥር 529/2013

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 377/2008 ለማስፈጸም ይህ መመሪያ ውጥቷል።

## ክፍል አንድ

### 1 አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ"የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ደንብን ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### 2 ትርጓሜ

በቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉት ቃላት ስለ ጥራጥሬ ምርቶች ግብይት የወጣውን ደንብ ቁጥር 377/2008 የተሰጠዉ የቃላት ትርጉም ለዚህ መመሪያ ያገለግላል::

## ክፍል ሁለት

### ስለ ጥራጥሬ ምርቶች አገልግሎት አሰጣጥ

### 3 የጥራጥሬ ምርቶች አዘገጃጀት

#### 3.1 የአቅርቦት የጥራጥሬ ምርቶች አዘገጃጀት

3.1.1 የጥራጥሬ ምርቶች የጥራት ደረጃውን ፣ የተፈጥሮ ቀለሙን በጠበቀ እና የዘር መጠን በተስተካከለ ሁኔታ መዘጋጀት አለበት ፣

3.1.2 የጥራጥሬ ምርቶች በሚዘጋጁበት ወቅት የእርጥበት መጠናቸዉ ከ13 በመቶ መብለጥ የለበትም፣

3.1.3 የጥራጥሬ ምርቶች በሚዘጋጅበት ጊዜ ከምርቱ ባህሪ ጋር የማይስማሙ እና የምርቱን ይዘት ከሚቀይሩ ከማንኛዉም ባዕድ ነገሮች የፀዱ መሆን አለባቸዉ፣

3.1.4 የጥራጥሬ ምርቶች በሚዘጋጅበት ጊዜ በጥራት ደረጃቸዉ እና በባህሪያቸዉ የተለያዩ፣ የአንዱን አካባቢ ምርት ከሌላ አካባቢ ምርት፣ የአንዱን ምርት

ዘመን ከሌላዉ ምርት ዘመን እንዲሁም በበልግ የተመረተ በመኸር ከተመረተ ምርት ጋር ሳያቀላቀል መዘጋጀት አለባቸዉ፣

3.1.5 የጥራጥሬ ምርቶች ዝግጅት ሲጠናቀቅ ይህን ለመቆጣጠር በህግ ስልጣን ለተሰጠው አካል የተዘጋጀዉ መጠንን፣ የተለዩ ብጣሪ እና ባዕድ ነገሮችን ለይቶ ማስቀመጥ አለበት፣

3.1.6 በመቆጣጠር በህግ ስልጣን የተሰጠዉ አካል አረጋግጦ የመሸኛ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል ፡፡

## 3.2 ለውጭ ገበያ የሚውሉ የጥራጥሬ ምርቶች አዘገጃጀት

3.2.1 የጥራጥሬ ምርቶች በማሽን ወይም በእጅ ለቀማ መዘጋጀት አለባቸዉ፣

3.2.2 የጥራጥሬ ምርቶች በየዓይነታቸዉ እና በጥራት ደረጃቸዉ ተለይተው ለውጪ ገበያ መዘጋጀት አለባቸዉ፣

3.2.3 የጥራጥሬ ምርቶቸ ለውጭ ገበያ በሚዘጋጁበት ወቅት ተመሣሣይ ባህሪና ዓይነት ካላቸው የጥራጥሬ ምርቶች ውጭ የአንዱን አካባቢ ምርት ከሌላ አካባቢ ምርት፣ የበልግ ምርት ከመኸር ምርት እንዲሁም የአንድን ምርት ዘመን ከሌላው ምር ት ዘመን ሳይቀላቅሉ ተለይተዉ መዘጋጀት አለባቸዉ ፣

3.2.4 የጥራጥሬ ምርቶች ለውጭ ገበያ በማሽን የሚዘጋጀት ከሆነ አግባብ ባለዉ ሴክተር መስሪያ ቤት በተረጋገጠ እና የብቃት ማረጋገጫ በተሰጠዉ የጥራጥሬ ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ መዘጋጀት አለበት፣

3.2.5 የተዘጋጁ የጥራጥሬ ምርቶቸ ወደ ውጭ እስከሚላኩ ድረስ አግባብ ባለዉ የሴክተር መ/ቤት ብቃቱ በተረጋገጠ የጥራጥሬ ማከማቻ መጋዘን መከማቸት አለበት፣

3.2.6 ለውጭ ገበያ የተዘጋጀ የጥራጥሬ ምርት አዘገጃጀት በተገቢዉ የጥራት ደረጃ መዘጋጀቱን በተዘጋጀለት ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ የተሰጠ የምስክር ወረቅት የሚያረጋግጥ መረጃ አያይዞ ማቅረብ አለበት፣

3.2.7 ለውጪ ገበያ የተዘጋጀ የጥራጥሬ ምርት ወደ ውጭ ከመላኩ በፊት የኢትዮጵያ የጥራጥሬ ምርት የጥራት ደረጃን ያሟላ ወይም የጥራት ደረጃ ያልወጣለት ከሆነ የገዢውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የጥራት ደረጃ ስለማሟላቱ በምርመራ መረጋገጥ አለበት፣

3.2.8 ማንኛዉም ለዉጪ ገበያ ተዘጋጀ ጥራጥሬ ምርት መያዣ ከረጢት ላይ አስፈላጊ መረጃዎችን መታተም /LABELING/ አለበት፣

3.2.9 የሀገር ውስጥ የምርት እጥረት ሲፈጠር ወደ ውጪ የሚላከው ምርት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ዉሳኔ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ እንዲዉል ይደረጋል፤

## 3.3 ለሀገር ዉስጥ ፍጆታ የሚዉሉ የጥራጥሬ ምርቶች አዘገጃጀት

3.3.1 ማንኛዉም ለፍጆታ የሚሆን የጥራጥሬ ምርት ወደ ገበያ ከመቅረቡ በፊት የጥራት ደረጀዉን ሊያበላሹ የሚችሉ በተባይ የተጠቁ፣ የጠቆሩ፣ የተፈጥሮ ቀለማቸዉን የቀየሩ እና በሻጋታ የበለዙ የጥራጥሬ ምርቶች ሳይቀላቀሉበት መዘጋጀት አለበት፣

3.3.2 ማንኛዉም ለሀገር ዉስጥ ፍጆታ የሚዉል የጥራጥሬ ምርት ሲዘጋጅ በሸማች ጤና ላይ ጉዳት ከሚያስከትሉ እንደመርዛማ ኬሚካሎች፣ የዕፅዋት ዘር፣ ነዳጅ እንዲሁም ቆዳና ሌጦ ከመሳሰሉት ባዕድ ነገሮች ነፃ በሆነ ሁኔታ መዘጋጀት አለበት፣

3.3.3 ተመሳሳይ የባህሪ አይነትና ዝርያ ካለቸዉ የጥራጥሬ ምርቶች ዉጪ ቀላቅሎ ያለማዘጋጀት፣

# 4 የጥራጥሬ ምርቶች ስለማጓጓዝ

## 4.1 የአቅርቦት ጥራጥሬ ምርቶች ስለማጓጓዝ

4.1.1 የጥራጥሬ ምርት የሚጫንበት ከረጢት ከኬሚካል የፀዳ እንዲሁም ለዚሁ አገልግሎት ብቻ የተዘጋጀና ለሌሎች አገልግሎቶች ጥቅም ላይ ያልዋለ መሆን አለበት፡፡

4.1.2 የጥራጥሬ ምርት የሚጓጓዝበት ማጓጓዣ የምርቱን ጥራት በቀላሉ ሊያበላሹ ከሚችሉ ማናቸዉም እንደ ነዳጅ፣ ኬሚካል፣ ቆዳና ሌጦ እና ከመሳሰሉት የፀዳና ከምርቱ ጋር የሚፃረር ባዕድ ነገር በደባልነት ያልጫነ መሆን አለበት፣

4.1.3 የጥራጥሬ ምርት የሚጓጓዝበት ማጓጓዣ እርጥበት፣ ፀሃይ እና አቧራ በማያስገባ ሁኔታ ተሸፍኖ መጓጓዝ አለበት ፣

4.1.4 በአቅራቢዎች ወደ ኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች የመጋዘን አገልግሎት ድርጅት መጋዘን የሚጓጓዘዉ ምርት አግባብነት ባለዉ የክልል አካል በተመደበ ተቆጣጣሪ የተረጋግጠ ሸኚ ሰነድ መረጃ በመያዝ ማጓጓዝ አለበት፣

4.1.5 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4.1.4 መሰረት አግባብ ባለዉ አካል በተመደበዉ ተቆጣጣሪ የሚሰጠዉ ሸኚ ሰነድ የሚከተሉትን መረጃዎች ማሟለት አለበት

ሀ/ የተሸከርካሪው ሠሌዳ ቁጥር

ለ/ የአሽከርካሪው ሙሉ ስም

ሐ/ የሚያጓጓዘዉ የጥራጥሬ ምርት አይነትና መጠን

መ/ ምርቱ የተሸኘበት ቀን

ሠ/ የምርቱ መነሻ እና መድረሻ ቦታ

ረ/ የምርቱ ባለቤት ሙሉ ስም

## 4.2 ለዉጭ ገበያ የሚቀርብ ጥራጥሬ ምርት ስለማጓጓዝ

4.2.1 የጥራጥሬ ምርት በኮንቴነር ሲላክ የሚጫንበት የኮንቴነር ወለልና ግድግዳዉ ከባዕድ ነገሮች እና ከኬሚካል ቅሪት የፀዳ ሆኖ የአየር ማስገቢያ ቀዳዳ ያለዉ መሆን ይኖርበታል፤

4.2.2 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4.2.1 የሚላኩ የጥራጥሬ ምርቶች ለቁጥጥር በሚያመች ሁኔታ ምርቱ በተዘጋጀበት ቦታ መታሸግ አለበት፤

4.2.3 የጥራጥሬ ምርት የሚጫንበት ከረጢት ከኬሚካል ንክኪ የፀዳ እንዲሁም ለዚሁ አገልግሎት ብቻ የተዘጋጀና ለሌላ አገልግሎት ያልዋለ መሆን አለበት፣

4.2.4 የጥራጥሬ ምርት የሚጓጓዝበት ተሽከርካሪ የምርቱን ጥራት ሊያበላሹ የሚችሉ እንደ ኬሚካል፣ ነዳጅ፣ ፈሳሽ፣ ቆዳ እና ሌጦ የመሳሰሉትን ያልጫነ መሆን አለበት፤

4.2.5 ከላኪዎች መጋዘን ወደ ወደብ የሚጓጓዘዉ የወጪ ጥራጥሬ ምርት በህግ ስልጣን በተሰጠዉ አካል ተረጋግጦና ታሽጎ ማጓጓዝ አለበት፡፡

4.2.6 ላኪዎች ከኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች የመጋዘን አገልግሎት ድርጅት መጋዘን ወደ ላኪዎች መጋዘን እና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ የሚጓጓዘዉ ምርት አግባብነት ባለዉ አካል በተመደበ የጥራጥሬ ምርቶች ሽኝት ሰራተኛ ሽኚ ሰነድ መረጃ በመያዝ ማጓጓዝ አለበት፤

4.2.7 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4.2.6 መሰረት አግባብ ባለዉ አካል የተመደበዉ የጥራጥሬ ምርቶች ሽኝት ሰራተኛ ሽኚ ሰነድበዚህ መመሪያ አንቀፅ 4.1.5 የተዘረዘሩትን ማሟለት አለበት፣

## 4.3 ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚዉል የጥራጥሬ ምርቶች ስለማጓጓዝ

4.3.1 የጥራጥሬ ምርት የሚጫንበት ከረጢት እንደ ኬሚካል፣ ነዳጅ፣ ፈሳሽ፣ቆዳ እና ሌጦ ከመሳሰሉት ንክኪ የፀዳ መሆን አለበት፤

4.3.2 የጥራጥሬ ምርት የሚጓጓዝበት ማጓጓዣ የምርቱን ጥራት በቀላሉ ሊያበላሹ ከሚችሉ እንደ ኬሚካል፣ ነዳጅ፣ ፈሳሽ፣ ቆዳ እና ሌጦ የመሳሰሉትን ያልጫነ መሆን አለበት፣

4.3.3 የጥራጥሬ ምርት የሚጓጓዝበት ማጓጓዣ እርጥበት፣ፀሃይ እና አቧራ በማያስገባ ሁኔታ ተሸፍኖ መጓጓዝ አለበት፣

4.3.4 ከመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላትና ከሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን በጅምላ ነጋዴዎች፣ በሸማች ህብረት ስራ ማህበራት እና በተቋማት የተገዙ ምርቶች ሲጓጓዙ አግባብነት ባለዉ የክልል አካል በተመደበ ተቆጣጣሪ ተረጋግጦ የተሰጠ ሽኚ ሰነድ በመያዝ መጓጓዝ አለበት፤

# 5 <u>የጥራጥሬ ምርት ስለማከማቸት</u>

5.1 የጥራጥሬምርቶች ማከማቸት ያለባቸዉ በአቅራቢዉ፣ በላኪዉ፣ በጅምላ ነጋዴዉ እና በህበረት ስራ ማህበራት በራሳቸዉ ይዞታ በሚገኘዉ መጋዘን ወይም ከሶስተኛ ወገን በኪራይ ዉል በአገኙት መጋዘን ብቻ መሆን አለበት፣

5.2 የጥራጥሬ ምርቶች የሚከማችበት መጋዘን ምርቱን በአግባቡ ለመደርደር የሚያስችል የጣራ ከፍታ ያለዉ እና በቂ አየር ማስተላለፍ የሚችል እንዲሁም የመጋዘኑ ወለል ከእርጥበት እና ከባዕድ ነግሮች የሚከላከል መሆን አለበት ፣

5.3 የአንድ አካባቢ የጥራጥሬ ምርት አይነት ከሌላዉ አካባቢ ምርት እንዲሁም በባህሪያቸዉ የተለያዩ የጥራጥሬ ምርት ጋር ሳይቀላቀል መከማቸት አለበት፣

5.4 የጥራጥሬ ምርቶች ሆነ ተብሎ እጥረት ለመፍጠር ማከማቸት የለባቸዉም፤

5.5 የጥራጥሬ ምርቶች የሚከማችበት መጋዘን ከምርቶቹ ጋር ተፃራሪ ከሆኑ እንደ ነዳጅ፣ ያልተፈቀዱ ኬሚካሎች፣ ቆዳና ሌጦ እና ከመሳሰሉት ንክኪ የፀዳ መሆን አለበት ፣

5.6 የጥራጥሬ ምርቶቸ ለፍጆታ ወይም ለገበያ ጥቅም ላይ እስከሚዉሉ ድረስ አግባብ ባለዉ የሴክተር መ/ቤት ብቃቱ በተረጋገጠ ማከማቻ መጋዘን መከማቸት አለበት ፡፡

## ክፍል ሦስት

## ጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ማዕከላት አከላለል፣ አሰራርእና አደረጃጀት

### 6 የመጀመሪያ ደረጃ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ማዕከላት ስለመከለልና የግብይት ቀናትን ስለመወሰን

6.1 የመጀመሪያ ደረጃ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ማዕከላት ከት/ቤት፣ ከጤና እና ከእምነት ተቋመት 100 ሜትር ርቀት በላይ ሆኖ መከለል አለበት፣

6.2 የመጀመሪያ ደረጃ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ማዕከላት የገበያ ቦታ ስፋት እንደ አካባቢዉ ተጨባጭ ሁኔታ እና እንደ ጥራጥሬ ምርቶች መጠን ሊወሰን ይችላል፤

6.3 የመጀመሪያ ደረጃ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ማዕከላት አከላለል የቀበሌ አስተዳደር ወሰንን ግምት ዉስጥ በማስገባት መካለል አለበት፣ የግብይት ማዕከላቱ በሁለት አጎራባች ወረዳዎች የሚያርፍ ሆኖ ሲገኝ በአጎራባች ወረዳዎች የሚገኙ አግባብነት ያላቸዉ አካላት አከላለሉን በጋራ ይወስናሉ

6.4 በአካባቢዉ በሚገኝ ቁሳቁስ በመጠቀም የተገነባ መሆን አለበት፣

6.5 የጥራጥሬ ምርቶች የገበያ ቦታ ከሌሎች የሰብል ምርቶች የተለየ ከሆነ ወይም ከሌሎች ምርቶች ጋር በአንድ የገበያ ማዕከል ከሆነ መገበያያ ቦታው ለብቻዉ መከለል ይችላል፤

6.6 የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማእከላት በጥራጥሬ ምርቶች ጥራት ላይ ተፅዕኖ ከሚያሳድሩ ሁኔታዎች ነፃ መሆን አለባቸዉ፣

6.7 የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት የሚካሄድበት ክልል፤ ዞን ወይም ወረዳ የአካባቢውን የግብይ ት ማዕከላት ብዛትና ሥርጭት ሲወስን የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ዉስጥ ማስገባት ይኖርበታል፣

(ሀ) ለጥራጥሬ አምራቾች፣ ጅምላ ነጋዴዎች፣ ሸማቾች ወይም ህብረት ሥራ ማኅበራት እንዲሁም ለአቅራቢዎች ያላቸዉ ቅርበት እና አማካይነት፣

(ለ) ተሽከርካሪን ለማስገባትና ለ ማስወጣት ያላቸው አመቺነት፣

(ሐ) አግባብነት ባለው የወረዳ አካል የገበያ መረጃ ሠሌዳ፣ መጫኛና ማራገፊያ፣ መደላድልን፣ ደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያና መፀዳጃ ቤትን ያጠቃለለ የጋራ መገልገያ መሣሪያዎች ሊያሟሉ የሚችሉ መሆኑ፣

(መ) ለእያንዳንዱ አቅራቢ፣ አቀነባባሪ እና የኅብርት ሥራ ማህበር መጠለያ ሊያሰራ የሚችል መሆን አለበት፣

( ሠ) ለእያንዳንዱ አምራች እና ቸርቻሪ የመገበያያ ቦታ ሊያሟላ የሚችል መሆን አለበት፣

6.8 የመጀመሪያ ደረጃ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ማዕከላትን የግብይት ቀን የክልሉ አግባብነት ያለዉ አካል እንደ አካባቢዉ ተጨባጭ ሁኔታ ሊወሰን ይችላል፡

## 7 <u>ሁለተኛ ደረጃ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት እርከን አከላለል፣ አሰራርና አደረጃጀት</u>

**ሁለተኛ ደረጃ የጥራጥሬ ምርቶች የግብይት እርከን የሚሰየመዉና የሚቋቋመዉ ግብይታቸዉ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ላልሆኑ ወይም ላልገቡ የጥራጥሬ ምርቶችን ለመገበያያነት የሚያገለግል ብቻ ሆኖ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፣**

7.1 ሁለተኛ ደረጃ የጥራጥሬ ምርቶች የግብይት እርከን ከት/ቤት፣ ከጤና እና ከሃይማኖት ተቋማት ከ100 ሜትር ባላነሰ ርቀት መከለል አለበት፣

7.2 ሁለተኛ ደረጃ የጥራጥሬ ምርቶች የግብይት እርከን ከሌሎች የሰብል ምርቶች እና ሸቀጣሸቀጦች ጋር በአንድ ቦታ ላይ የሚሆን ከሆነ ለጥራጥሬ ምርቶች ግብይት የሚዉለዉ ቦታ ለብቻዉ መከለል አለበት፣

*7.3* ሁለተኛ ደረጃ የጥራጥሬ ምርቶች የግብይት እርከን ሲመሰረት የቦታዉ ስፋት እንደ አካባቢዉ ተጨባጭ ሁኔታ ይወሰናል፣

*7.4* ሁለተኛ ደረጃ የጥራጥሬ ምርቶች የግብይት እርከን የሚከለልበት ቦታ በጥራጥሬ ምርቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከሚያሳድሩ ማናቸዉም ሁኔታዎች ነፃ መሆን አለበት፣

7.5 ሁለተኛ ደረጃ የጥራጥሬ ምርቶች የግብይት እርከን አከላለል የቀበሌ አስተዳደር ወሰንን ግምት ዉስጥ በማስገባት መካለል ይችላል፤ የግብይት ቦታዉ በሁለት አጎራባች ወረዳዎች መካከል የሚያርፍ ሆኖ ሲገኝ በአጎራባች ወረዳዎች የሚገኙ አግባብነት ያላቸዉ አካላት አከላለሉን በጋራ ይወስናሉ፣

7.6 ሁለተኛ ደረጃ የጥራጥሬ ምርቶች የግብይት እርከኑን የሚያስተዳድረዉ አግባብነት ያለዉ የክልል አካል የግብይት ቦታዉ በከተማ ክልል የሚገኝ ከሆነ ካርታ እና ፕላን ወይም በገጠር ቀበሌ የሚገኝ ከሆነ ደግሞ የቦታ ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዲኖረዉ ያደርጋል፣

7.7 አግባብነት ያለዉ የክልል አካል ሁለተኛ ደረጃ የጥራጥሬ ምርቶች የግበይት እርከን ብዛት እና ስርጭትን ሲወስን የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ዉስጥ ማስገባት አለበት፤

(ሀ) ለአምራቾች፣ ለአቅራቢዎች፣ ለጅምላ ነጋዴዎች፣ ለቸርቻሪዎች፣ ለአቀነባባሪዎች፣ ለኅ/ሥ/ ማህበራት እና ለላኪዎች ግብይት ያለዉ አመቺነት፣

**ለ**) ተሽከርካሪ ለማስገባት እና ለማስወጣት ያለዉ አመቺነት፣

(ሐ) የገበያ መረጃ ሰሌዳ፣ መጫኛ እና ማራገፊያ መደላድል፣ የደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ እና የፈሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ያለዉ መሆን አለበት፣

( መ) በአካባቢው በሚገኙ ቁሳቁሶች ወይም በግንብ ወይም በሽቦ በአስተማማኝ ሁኔታ የታጠረ መሆን አለበት።

(ሠ) ለጅምላ ነጋዴዎች፣ ለአቅራቢዎች፣ ለኅ/ሥ/ማህበራት፣ ለአቀነባባሪዎች ሼድ ሊያሰራ የሚችል መሆን አለበት፣

(ረ) ለቸርቻሪ ነጋዴዎች መገበያያ ቦታ ሊያሟላ የሚችል መሆን አለበት።

## ክፍል አራት

## የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ስርዓት

### 8 በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት የሚፈጸም የግብይት ስርዓት

8.1 የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ሻጭ በሆኑ አምራች አርሶ አደሮች እና አልሚ ባለሃብቶች እና ገዢ በሆኑ ሸማቾች/ አምራች ህብረት ስራ ማህበራት እንዲሁም በዘመኑ የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያለቸዉ አቅራቢዎች፣ አቀነባባሪዎች፣ ጅምላ እና ቸርቻሪ ነጋዴዎች መካከል ብቻ ግብይቱ የሚከናወን ይሆናል ፣

8.2 ግብይቱ በአቅራቢዎች፣ በሸማች ህብረት ስራ ማህበራት/ዩኒየኖች፣ በአቀነባባሪዎች እና በጅምላ እና ቸርቻሪ ነጋዴዎች ባለቤትነት በተያዘ በህግ ስልጣን በተሰጠዉ አካል ትክክለኛነቱ በተረጋገጠ ሚዛን ብቻ መከናወን አለበት፣

8.3 በዚህ አንቀፅ ንዑስአንቀፅ 8.2 የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ገዢዎች በሆኑ አቅራቢዎች፣ ሸማች ተቋማት፣ ጅምላ ነጋዴዎች እና አቀነባባሪዎች የግዥ ደረሰኝ አዘጋጅተዉ ከሻጭ ጋር ለሚያከናዉኑት ግብይት ደረሰኝ ማዘጋጀት አለባቸዉ፤

8.4 አግባብ ያለዉ የክልል፣ የዞን እና የወረዳ አካል የግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪ ባለሙያ መመደብ አለበት፣

8.5 የጥራጥሬ ምርቶችን ከመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት የገዛ አቅራቢ፣ ለላኪ፣ ለሌላ አቅ ራቢ፣ ለህብረት ስራ ማህበር፣ ለአቀነባባሪ፣ ለቸርቻሪ፣ ለጅምላ እና ለሸማቾች ተቋማት መልሶ መሸጥ የለበትም፣

8.6 በጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ደንብ እና በዚህ መመሪያ መሠረት የተያዙ የጥራጥሬ ምርቶች በግብይት ማዕከሉ በአቅራቢነት ወይም በቸርቻሪነት ወይም በሸማችነት ተቋማት ወይም በአቀነባባሪነት እንዲሠራ የብቃት ማረጋገጫ ለተሰጣቸዉ በጨረታ ይሸጣል፡፡

## 9 <u>በሁለተኛ ደረጃ ግብይት እርከን የሚፈጸም የግብይት ስርዓት</u>

**በሁለተኛ ደረጃ የጥራጥሬ ምርቶች የግብይት እርከን የሚፈጸመዉ ግብይታቸዉ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ላልገቡ የጥራጥሬ ምርቶች በክልል በሚገኙ ዞኖች እና ወረዳዎች በሚቋቋሙ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት እርከን የሚፈጸም ሆኖ፡-**

9.1 በሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት በድርድር ላይ ተመስርቶ ሲከናወን የዋጋ ስምምነት ላይ ሚደረሰዉ በገዢ እና ሻጭ መካከል የወቅቱን የገበያ ዋጋ መሰረት በማድረግ ይሆናል፣

9.2 የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ሻጭ በሆኑ አምራቾች ወይም ህብረት ስራ ማህበራት/ የኒየኖ ወይምአቅራቢዎች ወይም ጅምላ ነጋዴዎች እና ገዢ በሆኑ ላኪዎች ወይም አቀነባባሪዎች ወይም ሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራት ወይም ተቋማት ወይም ቸርቻሪዎች መካከል የሚከናወን ይሆናል፣

9.3 በህገ ወጥ መንገድ ሲንቀሳቀስ አግባብ ባለው የክልል አካል የተያዘ የጥራጥሬ ምርት ሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን ላይ ቀርቦ በጨረታ መሸጥ አለበት፤ የሽያጭ ገንዘቡም በህግ ዉሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ በዝግ አካዉንት ይቀመጣል፣

9.4 በሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን ሸማቾች የሆኑ ሆቴሎች፣ ዩኒቨርስቲዎች፣ ማረሚያ ቤቶች፣ የፖሊስ ተቋማት፣ መከላከያ ሰራዊት እና የመሳሰሉት ተቋማት ማንነታቸዉን የሚገልፅ ማስረጃ በማቅረብ መግዛት ይኖርባቸዋል፣

9.5 ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ የገቡ የጥራጥሬ ምርቶች በሁለተኛ ደረጃ ግብይት እርከን ላይ ግብይት አይካሄድባቸዉም፣

9.6 በሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን ላይ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት በወካይ ናሙና መሰረት በሽያጭ ዉል ስምምነት ሊፈጸም ይችላል፣

9.7 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 9.6 መሰረት ግብይቱ በሽያጭ ዉል ስምምነት የሚፈፀም ከሆነ፣-

(ሀ) ገዢ በሆኑ ላኪዎች እና ሻጭ በሆኑ አቅራቢዎች ወይም አምራቾች ወይም ህብረት ስራ ማበራት/ ዩኒየን መካከል የሚደረገዉ የዋጋ ዉል ስምምነት የሚወሰነዉ በገዢ እና ሻጭ መካከል በሚደረግ ድርድር ሆኖ የወቅቱን የገበያ ዋጋ መሰረት ያደረገ ይሆናል፤ እንዲሁም የንብርቱ እርክክብ የሚፈፀመዉ በዉል ስምምነታቸዉ መሰረት በሻጭ መጋዘንወይም በገዢ መጋዘን ወይም ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ላይ ሊሆን ይችላል፣

(ለ) ገዢ በሆኑ ሸማች ተቋማት ወይም ሸማች ህብረት ስራማህበራት ወይም ዩኒየን እና ሻጭ በሆኑ ጅምላ ነጋዴዎች ወይም አምራቾች መካከል በሚካሄደዉ የግብይት ዋጋ የሚወሰነዉ በገዢ እና ሻጭ መካከል በሚደረግ ስምምነት እና በወቅቱ የገበያ ዋጋ መሰረት ይሆናል፤ እንዲሁም የንብርቱ ርክክብ የሚፈፀመዉ በዉል ስምምነታቸዉ መሰረት በሻጭ መጋዘንወይም በገዢ መጋዘን ሊሆን ይችላል፣

(ሐ) ገዢ በሆኑ አቀነባባሪዎች እና ሻጭ በሆኑ አቅራቢዎች ወይም አምራቾች መካከል በሚደረገዉ የሽያጭ ዉል ስምምነት መሰረት ዋጋ የሚወሰነዉ በገዢ እና ሻጭ መካከል በሚደረግ ድርድር እና በወቅቱ የገበያ ዋጋ መሰረት ይሆናል፤ እንዲሁም የንብርቱ ርክክብ የሚፈፀመዉ በዉል ስምምነታቸዉ መሰረት በሻጭ መጋዘን ወይም በአቀነባባሪዉ መጋዘን ወይም ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ሊሆን ይችላል፣

(መ) የዉል ስምምነት ሰነዱ የጥራጥሬ ምርት አይነት፣ መጠን፣ ደረጃ፣ ግብይት የተካሄደበት ቀንና ቦታ፣ ምርቱ የሚቀርብበትና ክፍያ የሚፈፀምበት ቀንና ቦታ፣ የሁለቱን ተዋዋዎች አድራሻ እና ህጋዊ ማህተም ማካተት አለበት፣

9.8 አግባብነት ያለዉ የክልል አካል የግብይት እና የጥራት ተቆጣጣሪ ባለሙያዎችን መመደብ አለበት፣

## ክፍል አምስት

## የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ተዋናዮች እና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች መስፈርት

## 10 የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ተዋናዮች መስፈርት፣

### 10.1 የአቅራቢዎች መስፈርት

10.1.1 አግባብነት ያለዉ አካል ያወጣዉን የቴክኒክ መስፈርት ያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው ማከማቻ መጋዘን፣ ሚዛን እንዲሁም ደረጃዉን የጠበቀ ከረጢት እና የእርጥበት መለኪያ መሳሪያ ያሟላ መሆን አለበት፣

10.1.2 ወደ ኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች የመጋዘን አገልግሎት ድርጅት ለማቅረብ የገዛውን'፣ ያቀረበውን እና በመጋዘን በክምችት ያለዉን ምርት በአይነት እና በመጠን ለይቶ በወሩ መጨረሻ አግባብ ላለው የክልል አካል የሚያሳውቅበት የመረጃ ስርአት የዘረጋ መሆን አለበት፣

10.1.3 የአቅራቢነት ብቃቱ የተረጋገጠ ህጋዊ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ንግድ ፍቃድ ያለዉና ፍቃዱን ባወጣበት በሚገኝ ወረዳ የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት ብቻ የሚገዛ፣

10.1.4 በአንድ የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከል አንድ አቅራቢ ከአንድ በላይ ተወካይ መወከል የለበትም፣

10.1.5 ያዘጋጀዉን የአቅርቦት ጥራጥሬ ምርቶች መቅረብ በሚገባዉ የጊዜ ገደብ ብቻ ለኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች የመጋዘን አገልግሎት ድርጅት በማቅረብ የመሸጥ፣

### 10.2 የጅምላ ነጋዴዎች መስፈርት፣

10.2.1 አግባብነት ያለዉ አካል ያወጣዉን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው ማከማቻ መጋዘን፣ ሚዛን እንዲሁም ደረጃዉን የጠበቀ ከረጢት እና የእርጥበት መለኪያ መሳሪያ ያለዉ መሆን አለበት፣

10.2.2 ህጋዊ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ንግድ ፍቃድ ያለዉና ፍቃዱን ባወጣበት አካባቢ ለሚገኙ ሽማቾች እና ሸማች ተቋማት ለማቅረብ የተዘጋጀ፣

10.2.3 ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በክልሎች በሚቋቋም ሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን የገዛውን'፣ የሸጠዉን እና በመጋዘን በክምችት ያለዉን ምርት በአይነት እና በመጠን ለይቶ በወሩ መጨረሻ አግባብ ላለው የክልል አካል የሚያሳውቅበት የመረጃ ስርአት የዘረጋ፤

10.3 <u>የቸርቻሪ ነጋዴዎች መስፈርት</u>

10.3.1 ህጋዊ የጥራጥሬ ምርቶች የችርቻሮ ንግድ ፍቃድ ያለዉና ፈቃዱን ባወጣበት አካባቢ ለሚገኙ ሸማቾች ብቻ ለማቅረብ የተዘጋጀ፣

10.3.2 ከመጀመሪያ ደረጃ የገበያ ማዕከል የገዛውን፣ ለሸማቾች የሸጠዉን እና የቀረውን ምርት በዓይነት እና በመጠን ለይቶ አግባብነት ላለው አካል በመደበው ሸኚ ሠራተኛ በተጠየቀ ጊዜ መረጃውን ሊያሳይ የሚችል፣

10.3.3 አግባብነት ያለዉ አካል ያወጣዉን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው ሚዛን ያለዉ መሆን አለበት፣

10.4 . <u>የሸማች ህብረት ስራ ማህበራት/ዩኒየኖች መስፈርት</u>

10.4.1 አግባብነት ያለዉ አካል ያወጣዉን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው ሚዛን እና መጋዘን ያለዉ፣

10.4.2 በህግ ስልጣን በተሰጠዉ አካል የተመዘገበ ሆኖ የህጋዊ ሰዉነት የምስክር ወረቀት ያለዉ፣

10.4.3 አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለው ቋሚ አድራሻ እና ቦታ ያለው፤

10.4.4 ሰራተኛ በቋሚነት ያሰማራ መሆን አለባቸዉ፡፡

10.5 <u>የሸማች ተቋማት መስፈርት</u>

**ሸማች ድርጅቶች ወይም ተቋማት የጥራጥሬ ምርቶችን ለሆቴሎች፣ ለዩኒቨርስቲዎች፣ ለማረሚያ ቤቶችና ለፖሊስ ተቋማት፣ ለመከላከያ ሰራዊት ተቋማት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለቸዉ፡፡**

10.5.1 የተቋሙን ወይም የድርጅቱን ማንነት የሚገልዕ ማረጋገጫ ማስረጃ ያለዉ መሆን አለበት፣

10.5.2 ከተቋሙ ጋር ህጋዊ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ዉል የተዋዋለና የራሱ የንግድ ፍቃድ ያለዉ ሆኖ ምርቱን ለተቋሙ የሚያቀርብ መሆኑን የሚመሰክር የውል ሰነድ በመረጃነት ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት፡፡

10.6 <u>የላኪዎች መስፈርት</u>

10.6.1 አግባብነት ያለዉ አካል ያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ፣ የጥራጥሬ ምርቶችን ለውጪ ገበያ አዘጋጅቶ ለመላክ የሚያገለግል በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው

የማከማቻ መጋዘን፣ ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ እና ማሸጊያ ከረጢት ያለው መሆን አለበት፣

10.6.2 በህግ ስልጣን በተሰጠዉ አካል የተመሰከረለት በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል መሰረት ከሶስተኛ ወገን ያገኘው የምድር እና መለስተኛ ሚዛን እንዲሁም የእርጥበት መለኪያ መሳሪያ ያለው መሆን አለበት፤

10.6.3 የጥራጥሬ ምርቶችን በማዘጋጀት ሂደት በአካባቢው ማህበረሰብ እና በእንስሳት ጤንነት ላይ ጉዳት በማያስከትል ሁኔታ ቆሻሻን ለማስወገድ የሚያስችል አሰራር የዘረጋ መሆኑ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ መሆን አለበት፤

10.6.4 ወደ ውጪ ሀገር ለመላክ የገዛውን፣ ኮንትራት የገባዉንና በመጋዘን በክምችት ያለዉን ምርት በአይነት እና በመጠን በመለየት በወሩ መጨረሻ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚያሳውቅበት የመረጃ ስርዓት የዘረጋ መሆን አለበት፣

10.6.5 አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መልክ የተደራጀ ቋሚ አድራሻ እና አገልግሎት መስጫ ቢሮ ያለው መሆን አለበት፣

10.6.6 ከጥራጥሬ ምርቶች ግብይት እና ጥራት ጋር በተያያዘ እውቀት ያለው ባለሙያ በቋሚነት ያሰማራ መሆን አለበት፡፡

## 11 <u>የአገልገሎት ሰጪዎች መስፈርት፣</u>

### 11.1 <u>የምርት አዘጋጆች መስፈርት</u>

11.1.1 አግባብነት ያለዉ አካል ያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው ማከማቻ መጋዘን እና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ያለዉ መሆን አለበት፣

11.1.2 በህግ ስልጣን በተሰጠዉ አካል የተመሰከረለት በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው ሚዛን እና የእርጥበት መለኪያ መሳሪያ ያለው መሆን አለበት፤

11.1.3 የጥራጥሬ ምርቶች በማዘጋጀት ሂደት በአካባቢው ማህበረሰብ፣ እንስሳት ጤንነት ላይ ጉዳት በማያስከትል አኳሃን ቆሻሻን ለማስወገድ የሚያስችል አሰራር የዘረጋ መሆኑ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠለት መሆን አለበት፤

11.1.4 በባህሪያቸው የተለያዩ የጥራጥሬ ምርቶች አይነት እና ዝርያዎች እንደሚመረቱ በት አካባቢ ባህሪያ ለማዘጋጀት የሚያስችል አሰራር የዘረጋ መሆን አለበት፣

11.1.5 አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ቢሮ ያለዉ መሆን አለበት፣

11.1.6 ከጥራጥሬ ምርቶች ጥራት ጋር በተያያዘ እውቀት ያለው ባለሙያ በቋሚነት ያሰማራ መሆን አለበት ፡፡

### 11.2 <u>የምርት ማከማቻ መጋዘን አገልግሎት ሰጪ መስፈርት</u>

11.2.1 በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው የምርት ማከማቻ መጋዘን ያለው መሆን አለበት፣

11.2.2 በባህሪያቸው የተለያዩ የጥራጥሬ ምርቶች አይነቶችን፣ ዝርያዎች እና እንደሚመረቱት አካባቢ ባህሪያ በመለየት የመጋዘን አገልገሎት ለመስጠት የሚያስችል አሰራር የዘረጋ መሆን አለበት፣

11.2.3 በህግ ስልጣን በተሰጠዉ አካል የተመሰከረለት በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው ሚዛን ያለው መሆን አለበት፤

## 12 የአቀነባባሪዎች መስፈርት

12.1 አግባብነት ያለዉ አካል ያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው አግሮ ኢንዱስትሪ ያለዉ መሆን አለበት፣

12.2 በህግ ስልጣን በተሰጠዉ አካል የተመሰከረለት በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው ሚዛን እና የእርጥበት መለኪያ መሳሪያ እንዲሁም የኢንቨስትመን ፈቃድ ያለዉ እና ወደ ማምረት ሥራ የተሸጋገረ መሆን አለበት፣

12.3 የጥራጥሬ ምርቶች በማዘጋጀት ሂደት በአካባቢው ማህበረሰብ እና በእንስሳት ጤንነት ላይ ጉዳት በማያስከትል አኳሃን ቆሻሻን ለማስወገድ የሚያስችል አሰራር የዘረጋ መሆኑ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ መሆን አለበት፣

12.4 አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መልክ የተደራጀ ቋሚ አድራሻ እና አገልግሎት መስጫ ያለው መሆን አለበት፣

12.5 ከጥራጥሬ ምርቶች ግብይት እና ጥራት ጋር በተያያዘ እውቀት ያለው ባለሙያ በቋሚነት ያሰማራ መሆን አለበት፡

## ክፍል ስድስት

## የጥራጥሬ ምርት አምራቾች፣ የግብይት ተዋናዮች እና የአገልግሎት ሰጪ ግዴታዎች

### 13 አጠቃላይ ድንጋጌ

13.1 የግብይት ተዋናዮች የቦሎቄ፣የባቄላ እና የማሾ ጥራጥሬ ምርቶችን ከታህሳስ አንድ እስከ መጪዉ አመት ህዳር 30 ድረስ ሲሆን የሽምብራ፣ የአኩሪ አተር፣ የጓያ፣ የግብጦ እና የፒገን ቢን ምርቶች ከሆነ ከጥር አንድ እስከ መጪዉ አመት ታህሳስ 30 ድረስ በህግ በተወሰነ የገበያ መድረክ አቅርበዉ የመሸጥ፡፡

13.2 ማንኛዉም ግብይት ተዋናዮች ለግብይት ዘጋጃቸው የጥራጥሬ ምርቶች ውስጥ ጥራት ምርመራ አገልግሎት ናሙና እንዲሰጥ ሲጠየቅ ወካይ ናሙና በነፃ የማቅረብ፤

13.3 የጥራጥሬ ምርቶችን ከአምራች አካባቢዎች ወደ ኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች እና የመጋዘን አገልግሎት ድርጅት፣ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ሸማቾች ወይም ተቋማት በሚገኙበት አካባቢ ሲያጓጉዝ በሕግ ስልጣን በተሰጠው አስፈፃሚ አካል ኘሎምኘ ማሳሸግ እና ሕጋዊ መሸኛ ሰነድ የመያዝ፣

13.4 የየዕለቱን የጥራጥሬ ምርቶች ግዥና ሽያጭ አይነት እና መጠን፣ የዋጋ ዝርዝር እንዲሁም ለግብይት ስርዓት ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን መዝግቦ የመያዝና በሚመለከተው የመንግሥት አካል ሲጠየቅ የማሳወቅ እና የመተባበር፣

## 14 የአምራቾች ግዴታ

14.1 ማንኛውም አምራች ከራሱ ማሳ ያመረተውን የጥራጥሬ ምርት በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት ወይም በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ብቻ መሸጥ አለበት፣

14.2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 14.1 የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም አምራች ከራሱ ማሳ ያመረተውን የጥራጥሬ ምርት በግሉ ወይም አባል በሆነበት የኅብረትሥራ ማኅበር በኩል በቀጥታ ወደ ውጭ የመላክ ወይም በማቀነባበር ለገበያ ማቅረብ አለበት፤

14.3 በክምችት ወይም በማጓጓዝ ወቅት ያልተፈቀደ ኬሚካል አለመጠቀም ፤

14.4 በዚህ አንቀፅ ንዑስ በአንቀፅ 14.1፣14.2፣14.3 የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ አልሚ ባለሃብቱ የሚከተሉት ተጨማሪ ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

ሀ/ ያመረተውን የጥራጥሬ ምርት ወደ ግብይት ማዕከላት ለማቅረብም ይሁን ወደ ዉጪ ቀጥታ ለመላክ ሲፈልግ አልሚ መሆኑን፣ ያለማዉን የምርት አይነትና መጠን እንዲሁም ያለማበትን ቦታ የሚገልጽ በክልል የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ በኩል የተሰጠ ማረጋገጫ መረጃ መያዝ አለበት፣

ለ/ አልሚ ባለሀብቱ ከራሱ ማሳ ወይም በኮንትራት ዉል ካለማዉ የጥራጥሬ ምርት ዉጪ መግዛት፣ ማከማቸት፣ ማጓጓዝ እና መሸጥ የለበትም፤

ሐ/ የጥራጥሬ አልሚ ሆኖ በአካባቢዉ ካሉ አምራች አርሶ አደሮች ጋር በኮንትራት ዉል የሚያለማ ከሆነ የዉል ሰነዱን እና የምርቱን ዓመታዊ የምርት ግምት አሰርቶ አግባብነት ላለዉ የክልል አካል የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

## 15 የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ተዋናዮች ግዴታ

### 15.1 የአቅራቢዎች ግዴታ

15.1.1 እንዲሁም ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ያልገቡ የጥራጥሬ ምርቶችን በሁለተኛ ደረጃ የአቅራቢነት ብቃቱ ተረጋግጦ ህጋዊ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ንግድ ፍቃድ ያለዉና ፈቃዱን ባወጣበት ወረዳ የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት ብቻ ከአምራች መግዛት አለበት፣

15.1.2 አግባብነት ያለዉ አካል ያወጣዉን የቴክኒክ መስፈርት ያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው ማከማቻ መጋዘን፣ ሚዛን እንዲሁም ደረጃዉን የጠበቀ ከረጢት እና የእርጥበት መለኪያ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

15.1.3 ያዘጋጀዉን ጥራጥሬ ምርቶች አቅርቦት መቅረብ በሚገባዉ የጊዜ ገደብ ብቻ ለኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች የመጋዘን አገልግሎት ድርጅት የማቅረብ እና ምርትን አላግባብ በመጋዘን ያለማከማቸት፣

15.1.4 ከመጀመሪያ ደረጃ የገበያ ማዕከላት የሚያጓጉዟቸውን የጥራጥሬ ምርቶች አግባብ ባለው የክልል አካል በተመደቡ የቁጥጥር ባለሙያዎች ለምርመራ ሲጠየቁ ማስመርመር ይኖርበታል፣

15.1.5 ከመጀመሪያ ደረጃ የገበያ ማዕከላት የገዛዉን የጥራጥሬ ምርቶች ለኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች የመጋዝን አገልግሎት ድርጅት ማቅረብ እና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የመሸጥ የግብይት እርከን መሸጥ አለበት፣

15.1.6 የጥራጥሬ ምርቶችን ለሌላ አገልግሎት በዋለ እና ንጹህ ባልሆነ ከረጢት ያለማጓጓዝና ያለማከማቸ፣

15.1.7 አንድ አቅራቢ በአካባቢዉ ፍትህ ፅ/ቤት የተረጋገጠ ዉክልና በተሰጠዉ ተወካይ አማካኝነት በአካባቢዉ ከሚገኙት የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት ሁሉ ምርት መግዛት ይችላል፤ ሆኖም በአንድ የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከል ከአንድ በላይ ተወካይ መመደብ ወይም ማሰማራት የለበትም፤

15.1.8 የአንድን አካባቢ የጥራጥሬ ምርቶች ከሌላ አካባቢ የጥራጥሬ ምርቶች እንዲሁም የአንድን ምርት ዘመን የጥራጥሬ ምርቶች ከሌላ ምርት ዘመን የጥራጥሬ ምርቶች ጋር ሳያደባልቅ መከዘን እና መሸጥ አለበት ፣

15.1.9 ለጥራጥሬ ምርቶች ማከማቻነት በተዘጋጀና ከምርቱ ጋር ተፃራሪ ካሆኑ ከነዳጅ፣ ቆዳና ሌጦ እና ካለተፈቀዱ ኬሚካሎች ንኪኪ ነፃ በሆነ መጋዘን ውስጥ ብቻ ማከማቸት አለበት፤

15.1.10 ምርቱን በሚያጓጉዝበት ወቅት ያልተፈቀዱ ኬሚካሎችን አለመጠቀም፤

15.1.11 ከመጀመሪያ ደረጃ የገበያ ማዕከላት የገዛውን ወደ ኢትዩጵያ የግብርና ምርቶች የመጋዘን አገልግሎት ድርጅት ያቀረበውን እና በመጋዘን በክምችት የሚገኘዉን የጥራጥሬ ምርት ዓይነት እና መረጃ ለይቶ በመያዝ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ አግባብነት ባለው የክልል አካል ሲጠየቅ ማሳወቅ አለበት፤

15.1.12 በክልሉ ጉዳዩ የሚመለከተዉን አካል ሳያስፈቅድ በአንድ አካባቢ ዉስጥ በሚገኝ ሌላ ቦታ ላይ ተጨማሪ የጥራጥሬ ምርት ንግድ ስራ የሚካሄድበት ድርጅት ማቋቋም የለበትም፣

15.1.13 የንግድ ፍቃዱን በማንኛዉም መልኩ ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ የለበትም፣

15.1.14 ማንኛውም አቅራቢ ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት የገዛውን የጥራጥሬ ምርት ወደ ኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች የመጋዘን አገልግሎት ድርጅት እና ሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን ሲያጓጉዝ አግባብነት ባለዉ የክልል አካል በተመደበ ተቆጣጣሪ የተረጋገጠ ሸኚ ሰነድ በመያዝ ማጓጓዝ አለበት፣

15.1.15 የጥራጥሬ ምርቶችን ሲዘጋጅ በአካባቢ ማህበረሰብ እና በእንስሳት ጤንነት ላይ ጉዳት በማያስከትል ሁኔታ ቆሻሻን ማስወገድ የሚያስችል አሰራር መዘርጋት አለበት፤

15.1.16 ማንኛውም አቅራቢ ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት የገዛውን የጥራጥሬ ምርቶችን ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ከሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን በማቅረብ ለላኪዎች ብቻ መሸጥ አለበት፣

15.1.17 የጥራጥሬ ምርቶች ግብይትን ለማስፈፀም የወጣውን ደንብና መመሪያ የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

## 15.2 የላኪዎች ግዴታዎች

15.2.1 የጥራጥሬ ምርቶችን ከኢትዩጵያ ምርት ገበያ ወይም ከሁለተኛ ደረጃ የጥራጥሬ ምርቶች የግብይት እርከን ከአቅራቢዎች መግዛት አለበት ፤

15.2.2 ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ከሁለተኛ ደረጃ የጥራጥሬ ምርቶች የግብይ ት እርከን የገዛውን የጥራጥሬ ምርት በተፈቀደለት መጋዘን እና ኢንዱስትሪ ብ ቻ ማከማቸት እና ማዘጋጀት አለበት፤

15.2.3 አንድ ላኪ ድርጅት ከገዢ ኩባንያ ጋር የኮንትራት ሽያጭ ውል ከተዋዋለ በኂላ በ24 ሰዓት ባልበለጠው ጊዜ ውስጥ ውሉን ለብሔራዊ ባንክ በማቅረብ፣ የማጸደቅ እና ከአስራ አምስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አግባብነት ላለው አካል የውል ሰነዱን በማቅረብ ማስመዝገብ አለበት፣

15.2.4 ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ከሁለተኛ ደረጃ የጥራጥሬ ምርቶች የግብይት እርከን ገዝቶ ያዘጋጀውን የጥራጥሬ ምርት ወደ ውጪ ከመላኩ በፊት በሃገሪቱ የጥራት ደረጃ መሠረት ወይም የጥራት ደረጃ ያልወጣለት ከሆነ በገዥው የጥራትና ደረጃ ፍላጎት መሠረት መዘጋጀቱ በምርመራ መረጋገጥ አለበት፤

15.2.5 ወደ ውጪ በሚላከው የጥራጥሬ ምርቶች መያዣ ከረጢት ላይ የምርቱን ዓይነት፣መጠን፤የጥራት ደረጃ፤

የላኪ ድርጅቱን ስም፣ በኢትዮጵያ የተመረተ መሆኑን እንዲሁም የሚሄድበ ትን አገር እና የገዢ ኩባንያውን ስም የሚገልጽ ጽሁፍ ማሳተም አለበት፣

15.2.6 የጥራጥሬ ምርቶች መያዣ ከረጢቶችን ባዕድ ከሆኑ እንደ ነዳጅ፣ ቅባት፣ ኬሚካሎች፣ ቆዳና ለየጦ የመሳሰሉ ጥራትን ከሚያጓድሉ ባዕድ ነገሮች ጋር ማከማቸት ወይም ማጓጓዝ የለበትም፤

15.2.7 ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ከሁለተኛ ደረጃ ግብይት እርከን የገዛውን፣ ወ ደ ውጪ የላከውን እና በመጋዘን በክምችት የሚገኘዉን የምርት ዓይነት እና መጠን ለይቶ በመያዝ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ አግባብነት ባለው አካል ሲጠየቅ ማሳወቅ አለበት፤

15.2.8 አግባብነት ያለው አካል የመደባቸው ተቆጣጣሪዎች አስፈላጊ በሆነበት በማንኛውም ጊዜ ሁሉ ወደ ላኪው ድርጅት ገብተው ቁጥጥር እንዲያካሄዱ መተባበር አለበት፡፡

15.2.9 በማከማቻ እና በማዘጋጃ ኢንዱስትሪው የሚገኘውን ምርት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለሚያካሂደው የግብይትና የምርት ጥራት ቁጥጥር እንዲሁም የክምችት ቆጠራ ሥራ በሚያመች መንገድ በየምርት ዓይነቱ ለይቶ ማዘጋጀት አለበት ፤

15.2.10 ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ከሁለተኛ ደረጃ እርከን የገዛውን የጥራጥሬ ምርቶች ከአንድ የምርት ዘመን በላይ ማከማቸት የለበትም፣

15.2.11 አግባብነት ላለው አካል በቅድሚያ አሳውቆ እስካል ተፈቀደለት ድረስ ከኢትዮ ጵያ ምርት ገበያ ወይም ከሁለተኛ ደረጃ እርከን የገዛውን የጥራጥሬ ምርት ቀ ድሞ ካስመዘገበው እና ከተፈቀደለት የማዘጋጃ ኢንዱስትሪ እና የማከማቻ መ ጋዘን ውጪ ማዘጋጀት ወይም ማከማቸት የለበትም፣

15.2.12 ምርቱን በሚከማችበት እና በሚያጓጉዝበት ወቅት ያልተፈቀዱ ኬሚካሎችን መጠቀም የለበትም፤

15.2.13 ላኪ ድርጅት የገዛዉን የጥራጥሬ ምርት በሚያዘጋጅበት ወቅት የሚያገኘዉንና ለዉጪ ገበያ የማይዉለዉን ተረፈ ምርት/ብጣሪ ህጋዊ የጥራጥሬ ምርት ጅምላ ንግድ ፍቃድ ላላቸዉ ግለሰቦችና ድርጅቶች እንዲሁም ለአቀነባበሪዎች ብቻ መሸጥ አለበት፣

15.2.14 ወደ ውጪ የሚላከው የጥራጥሬ ምርት በሀገር ውሰጥ እጥረት መኖሩ በመንግስት ሲወሰን ለታለመለት አላማ ማቅረብ አለበት፤

15.2.15 አግባብነት ያለዉ አካል ያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ የጥራጥሬ ምርቶችን ለውጪ ገበያ አዘጋጅቶ ለመላክ የሚያገለግል በባለቤትነት የያዘው

ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው የማከማቻ መጋዘን፣ ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ እና ከረጢት ማሟላት አለበት፣

15.2.16 በህግ ስልጣን በተሰጠዉ አካል የተመሰከረለት በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው የምድር እና መለስተኛ ሚዛን እንዲሁም የእርጥበት መለኪያ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

15.2.17 የጥራጥሬ ምርቶች በማዘጋጀት ሂደት በአካባቢው ማህበረሰብ እና እንስሳት ጤንነት ላይ ጉዳት በማያስከትል አኳሃን ቆሻሻን ማስወገድ አለበት፤

15.2.18 ከኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች የመጋዘን አገልግሎት ድርጅት መጋዘን ወደ ላኪዉ ማዘጋጃ ወይም መጋዘን ወይም ከሁለተኛ ደረጃ እርከን ገዝቶ የሚጓጓዘዉ ምርት በንግድ ሚኒስቴር በሸኚ ባለሙያ ወይም በክልል ግብይት ተቆጣጣሪ ባለሙያ የሸኚ ሰነድ መረጃ በመያዝ ማጓጓዝ አለበት፡፡

15.2.19 የንግድ ፍቃድን በማንኛዉም መልኩ ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ የለበትም፣

## 15.3 የጅምላ ነጋዴዎች ግዴታ

15.3.1 አግባብነት ያለዉ አካል ያወጣዉን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው ማከማቻ መጋዘን፣ ሚዛን እንዲሁም ደረጃዉን የጠበቀ ከረጢት ማሟላት አለበት፣

15.3.2 ህጋዊ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ንግድ ፍቃድና ባወጣበት አካባቢ ለማቅረብ የተዘጋጀ መሆን አለበት፣

15.3.3 ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ከመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት የጥራጥሬ ምርቶች መግዛት አለበት፤

15.3.4 ከምርት ገበያ ወይም ከመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት የገዛውን የጥራጥሬ ምርት ከተመረተበት አካባቢ ውጪ በሚገኝና እንዲሰራበት በተፈቀደለት አካባቢ ለሚገኙ ቸርቻሪዎች፣አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና የሸማቾች ኅብረት ስራ ማህበራት ብቻ መሸጥ አለበት፣

15.3.5 ከምርት ገበያ እና ከመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት የገዛውን የጥራጥሬ ምርት እንዲሰራበት በተፈቀደለት አካባቢ ለሚገኙ ተጠቃሚዎች ጥራትና ደረጃው እንደተጠበቀ በወቅቱ ማቅረብ አለበት፤

15.3.6 የጥራጥሬ ምርቶች መያዣ ከረጢቶችን ባዕድ ከሆኑ ነገሮች እንደ ነዳጅ፣ ቅባት፣ ኬሚካሎች፣ ቆዳና ሌጦ ጥራትን ከሚያጓድሉ ነገሮች ጋር ማከማቸት ወይም ማጓጓዝ የለበትም፤

15.3.7 ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ከመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት የገዛዉን የጥራጥሬ ምርቶች እጥረትን ሊያስከትል በሚችል ደረጃ ማከማቸት የለበትም፤

15.3.8 ባከማቸበት ወይም በሚያጓጉዝበት ወቅት ያልተፈቀዱ ኬሚካሎችን መጠቀም የለበትም፤

15.3.9 ከምርት ገበያ ወይም ከመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት የገዛውን፣ወደ ተፈቀደለት አካባቢ ወስዶ ያከፋፈለውን እና በመጋዘን በክምችት የሚገኘዉን የጥራጥሬ ምርት ዓይነት እናመጠን ለይቶ በመያዝ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ አግባብነት ላለው አካል ሲጠየቅ ማሳወቅ አለበት ፤

15.3.10 የንግድ ፍቃድን በማንኛዉም መልኩ ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ የለበትም

15.3.11 የሀገሪቱ የጥራጥሬ ምርቶቸ ጥራትና ግብይት ከሚጎድፉ ማናቸዉም ድርጊቶች መቆጠብ አለበት ፣

15.3.12 ጅምላ ነጋዴዎች ሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን ለመሸጥ በገቡት ዉል መሰረት ምርቱ ማስረከብ አለበት፣

15.3.13 ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ግብይት ስርዓት የገቡ የጥራጥሬ ምርቶችን ከመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት መግዛት የለበትም፤

15.3.14 የጥራጥሬ ምርቶችን ግብይት ለማስፈፀም የወጡ ደንብና መመሪያ የማክበር ግዴታዎች አለበት፣

## 15.4 <u>የሽማች ህብረት ስራ ማህበራት/ዩኒየኖች ግዴታ</u>

15.4.1 አግባብነት ያለዉ አካል ያወጣዉን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው ሚዛን እና መጋዘን ማሟላት አለበት ፣

15.4.2 የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበሩ አካባቢ ለሚገኙ ሸማቾች ብቻ ማቅረብ አለበት ፣

15.4.3 ቋሚ አድራሻ እና መሸጫ ቦታ ማሟላት አለበት፤

15.4.4 ባለሙያ በቋሚነት ማሰማራት አለበት፣

15.4.5 የጥራጥሬ ምርቶችን ከመጀመሪያ ደረጃ የገበያ ማዕከላት ወይም ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ከሁለተኛ ደረጃ እርከን የጥራጥሬ ምርቶች የግብይት ማዕከላት ብቻ መግዛት አለባት፣

15.4.6 ከመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት ወይም ከምርት ገበያ ወይም ከሁለተኛ ደረጃ እርከን የገዛውን የጥራጥሬ ምርት ከተመረተበት አካባቢ ውጪ በሚገኝና እንዲሰራበት በተፈቀደለት አካባቢ ለሚገኙ ሸማቾች ማቅረብና መሸጥ አለበት፣

15.4.7 የጥራጥሬ ምርቶች መያዣ ከረጢቶችን ባዕድ ከሆኑ ነገሮች እንደ ነዳጅ፣ቅባት፣ ኬሚካሎች፣ቆዳና ሌጦ የመሳሰሉት ጥራትን ከሚያጓድሉ ነገሮች ጋር ማከማቸት ወይም ማጓጓዝ የለበትም ፡፡

15.4.8 የጥራጥሬ ምርቶችን ግብይት ለማስፈፀም የወጡ ደንብና መመሪያ የማክበር ግዴታ አለባቸዉ ፡፡

## 15.5 የሸማች ተቋማት ግዴታዎች

**ሸማች ድርጅት ወይም ተቋማት የጥራጥሬ ምርቶችን ለሆቴል፣ ለዩኒቨርስቲ፣ለማረሚያ ቤቶችና ፖሊስ ተቋማት፣ ለመከላከያ ሰራዊት የሚገዙት ተቋማት የሚከተሉትን ግዴታዎች ማሟላት አለባቸዉ፡፡**

15.5.1 የጥራጥሬ ምርቶችን ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ከሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን መግዛትና ማቅረብ አለበት፣

15.5.2 የጥራጥሬ ምርቶች መያዣ ከረጢቶችን ባዕድ ከሆኑ ነገሮች ነዳጅ፣ቅባት፣ ኬሚካሎች፣ ቆዳና ሌጦ ከመሳሰሉት ጥራትን ከሚያጓድሉ ነገሮች ጋር ማከማቸት ወይም ማጓጓዝ የለበትም ፤

15.5.3 የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ዉል ለመፈፀም ንግድ ፍቃድ ያለዉ ሆኖ በተቋሙ የሚቀርብ የግብይት ዉለ ሰነድ መረጃ መያዝ አለበት፣

15.5.4 የሀገሪቱ የጥራጥሬ ምርቶች ጥራትና ግብይት ከሚጎድፉ ማናቸዉም ድርጊቶች መቆጠብ አለበት፣

15.5.5 ሸማች ተቋማት ከሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን ለመግዛት በገቡት ዉል መሰረት ምርቱ መቀበልና ክፍያ መፈጸም አለበት ፣

15.5.6 የጥራጥሬ ምርቶችን ግብይት ለማስፈፀም የወጡ ደንብና መመሪያ የማክበር ግዴታ አለባቸዉ ፡፡

### 15.6 <u>የቸርቻሪ ነጋዴዎች ግዴታ</u>

15.6.1 ህጋዊ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ንግድ ፍቃድ ባወጣበት አካባቢ ብቻ የመሸጥ፣

15.6.2 የጥራጥሬ ምርቶችን ከመጀመሪያ ደረጃ የገበያ ማዕከላት ወይም ከጅምላ ነጋዴዎች ብቻ የመግዛት፤

15.6.3 የጥራጥሬ ምርቶችን ለሸማቾች ብቻ የመሸጥ፤

15.6.4 የጥራጥሬ ምርቶች መያዣ ከረጢቶች ባዕድ ከሆኑ ነገሮች እንደ ነዳጅ፣ቅባት፣ ኬሚካሎች፣ቆዳና ሌጦ ከመሳሰሉት ጥራትን ከሚያጓድሉ ነገሮች ጋር ማከማቸትና ማጓጓዝ የለበትም

15.6.5 የጥራጥሬ ምርቶችን ግብይት ለማስፈፀም የወጡ ደንብና መመሪያ ማክበር አለበት፣

15.6.6 የንግድ ፍቃድን በማንኛዉም መልኩ ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ የለበትም ፡፡

### 15.7 <u>የአቀነባባሪዎች ግዴታ</u>

15.7.1 አግባብነት ያለዉ አካል ያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው አግሮ ኢንዱስትሪ ያለዉ መሆን አለበት፣

15.7.2 በህግ ስልጣን በተሰጠዉ አካል የተመሰከረለት በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው ሚዛን እና የእርጥበት መለኪያ መሳሪያ እና የኢንቨስትመን ፈቃድ ያለዉ ሆኖ ወደ ማምረት ተግባር የተሸጋገረ መሆን አለበት፣

15.7.3 የጥራጥሬ ምርቶችን ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት ወይም ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ከሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን መግዛት አለበት ፤

15.7.4 ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት ወይም ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ከሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን የገዛዉን የጥራጥሬ ምርቶች በኢንዱስትሪ በማቀነባበር ለገበያ ማቅረብ አለበት ፤

15.7.5 ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት እና ከምርት ገበያ ወይም ከሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን የገዛውን፣ በማቀነባበር ለገበያ ያቀረበውን እና በመጋዘን በክምችት የሚገኘዉን የጥራጥሬ ምርት ዓይነት እና መጠን ለይቶ በመያዝ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ አግባብነት ባለው አካል ሲጠየቅ ማሳወቅ አለበት፤

15.7.6 የጥራጥሬ ምርቶችን በማቀነባበር ሂደት የሚፈጠሩ ለአገልግሎት የማይዉሉ ተረፈ ምርቶችን በአካባቢው ማህበረሰብ እና እንስሳት ጤና ላይ ጉዳት በማያስከትል ሁኔታ ማስወገድ አለበት ፣

15.7.7 የጥራጥሬ ምርቶችን ግብይት ለማስፈፀም የወጡ ደንብና መመሪያ ማክበር አለበት፣

15.7.8 የንግድ ፍቃድን በማንኛዉም መልኩ ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ የለበትም ።

15.7.9 የሀገሪቱ የጥራጥሬ ምርቶች ጥራትና ግብይት ከሚጎድፉ ማናቸዉም ድርጊቶች መቆጠብ አለበት፣

15.7.10 አቀነባበሪዎች ከሁለተኛ ደረጃ እርከን ግብይት ማዕከላትን ለመግዛት በገቡት ዉል መሰረት ምርቱ መቀበልና ክፍያ መፈጸም አለባቸዉ፣

15.7.11 አቀነባባሪዎች ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃነት የሚያሰፈልጋቸዉን ከሚያመርቱ አዉትግሮውሮች ላይ የጥራጥሬ ምርቶችን በቀጥታ የሚቀርብበት የግብይት ሥርአት መጠቀም አለባቸዉ ።

## 16 የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ግዴታ

### 16.1 የማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች ግዴታ

16.1.1 አግባብነት ያለዉ አካል ያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው ማከማቻ መጋዘን እና መዘጋጃ ኢንዱስትሪ ያለዉ መሆን አለበት ፣

16.1.2 በህግ ስልጣን በተሰጠዉ አካል የተመሰከረለት በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው ሚዛን እና የእርጥበት መለኪያ መሳሪያ ያሟላ መሆን አለበት፤

16.1.3 የጥራጥሬ ምርቶች በማዘጋጀት ሂደት በአካባቢው ማህበረሰብ እና እንስሳት ጤንነት ላይ ጉዳት በማያስከትል አኳሃን ቆሻሻን ለማስወገድ የሚያስችል

አሰራር የዘረጋ መሆኑ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ መሆን አለበት፤

16.1.4 በባህሪያቸው የተለያዩ የጥራጥሬ ምርቶች አይነት እና ዝርያዎች እንደሚመረ ቱበት አካባቢ ባህሪያት ለማዘጋጀት የሚያስችል አሰራር የዘረጋ መሆን አለበት ፣

16.1.5 የወጪ ጥራጥሬ ምርቶችን የሚያዘጋጅ ኢንዱስትሪ ምርት ለማዘጋጀት የ ሚያስፈጉ መስፈርቶችን ያሟላና ጥራቱን በጠበቀ መንገድ ማዘጋጀት የሚያ ስችል ብቃት ያለው መሆኑን በህግ ሥልጣን በተሰጠዉ አካል ማረጋገጥ አለበት ፣

16.1.6 ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ከላኪዎች የተረከባቸውን የጥራጥሬ ምርቶች ዓይነት፣ ዝርያ እና የጥራት ደረጃ ጠብቆ ስለመዘጋጀቱ ማረጋገጫ መስጠትና በገባው ውል ስምምነት መሠረት በወቅቱ ለባለቤቱ ማስረከብ አለበት፤

16.1.7 ከላኪዎች የተረከበውን የጥራጥሬ ምርት እስከሚዘጋጅ እና ያዘጋጀውን ምርት ለባለቤቱ እስከ ሚያስረክብ ድረስ የሚያከማችበትን መጋዘን እና የሚገለገልባቸውን ከረጢቶ የምርት ጥራትን ከሚያጓድሉ ባዕድ ነገሮች ንክኪ ነፃ ማድረግ አለበት፣

16.1.8 ከላኪዎች የተረከበውን፣ያዘጋጀውን እና ለባለቤቱ ያስረከበውን የጥራጥሬ ምርት ዓይነት እና መጠን ለይቶ በመያዝ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ አግባብነት ባለው አካል ሲጠየቅ ማሳወቅ አለበት ፡፡

## 16.2 <u>የማከማቻ መጋዘን አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ግዴታ</u>

16.2.1 በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን የተገኘ ደረጃውን የጠበቀ በቂ ማከማቻ መጋዘን ያለው መሆን አለበት፤

16.2.2 ምርቱን ባከማቸበት መጋዝን ያልተፈቀደ ኬሚካሎችን መጠቀም የለበትም ፣

16.2.3 የአንድን አካባቢ የጥራጥሬ ምርቶች ከሌላ አካባቢ የጥራጥሬ ምርቶች እንዲሁም የአንድን ምርት ዘመን የጥራጥሬ ምርቶች ከሌላ ምርት ዘመን የጥራጥሬ ምርቶች ጋር ሳያደባልቅ መከዘን አለበት፤

16.2.4 ተረክቦ ያከማቸውን የጥራጥሬ ምርት ዓይነት፣ መጠን እና የጥራት ደረጃ ጠብቆ በገባው የውል ስምምነት መሠረት በወቅቱ ለባለቤቱ ማስረከብ አለበት፣

16.2.5 ለማከማቸት የተረከበውን፣ ለባለቤቱ መልሶ ያስረከበውን እና በመጋዘን በክምችት የሚገኘዉን የጥራጥሬ ምርት ዓይነት እና መጠን ለይቶ በመያዝ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ አግባብነት ባለው አካል ሲጠየቅ ማሳወቅ አለበት ::

## 16.3 የአጓጓዦች ግዴታ

16.3.1 የሚያጓጓዘዉን የጥራጥሬ ምርቶች አይነትና መጠን አጓጓዡ አረጋግጦ መረከብ አለበት ፣

16.3.2 ማንኛዉም የጥራጥሬ ምርትን አጓጓዥ ከአቧራ እና ከፀሀይ እንዲሁም ከዝናብ በማያስገባ ሁኔታ ማጓጓዝ አለበት፣

16.3.3 የጥራጥሬ ምርትን ከመጓጓዙ በፊት በግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪዎች የመሸኛ ሰነድ መረጃ ይዞ ማጓጓዝ አለበት፣

16.3.4 የጥራጥሬ ምርትን ጥራት ከሚያጓድሉ እንደ ኬሚካል፤ ፈሳሽ፣ ነዳጅ፣ እንስሳት፣ ቆዳና ሌጦ የመሳሰሉትን ባዕድ ነገሮችን ቀላቅሎ ማጓጓዝ የለበትም፣

16.3.5 የጥራጥሬ ምርትን እንዲያጓጉዝ ከተፈቀደለት መስመርና ቦታ ዉጪ ማጓጓዝ የለበትም፣

16.3.6 የጥራጥሬ ምርትን እንዲያጓጉዝ በተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ማድረስ አለበት፣

16.3.7 የጥራጥሬ ምርቶችን ግበይት ለማስፈፀም የወጡ ደንቦች እና መመሪዎችን ማክበር አለበት ፡

# ክፍል ሰባት

## የጥራጥሬ ምርቶች ግብይትና ጥራት ቁጥጥር፣

የጥራጥሬ ምርቶች ግብይትና ጥራት ቁጥጥር ሥራ አግባብነት ባለው የፌደራል ወይም የክልል አካ ል በሚመደቡ የግብይትና ጥራት ቁጥጥር ባለሙያዎች አማካኝነት የሚከናወን ሲሆን በተጨማሪም በክ ልል፣ በዞን፣ በወረዳ እና ቀበሌ ላይ በሚገኙ አስፈላጊነታቸው በታመነባቸው ቦታዎች ላይ የጥራጥሬ ም ርቶች ግብይትና ጥራት መቆጣጠሪያ ጣቢያዎን ማቋቋም እና ተቆጣጣሪዎችን መመደብ ይችላሉ።

## 17 የጥራጥሬ ምርቶች ግብይትና ጥራት ቁጥጥር ባለሙያዎችን ስለመመደብ

### ሀ/ የግብይት ባለሙያ

1. ስለ ጥራጥሬ ምርቶች ግብይት በቂ ዕውቀት ያለውና በመልካም ስነምግባሩ የተመሰከረለት መሆን አለበት፤
2. ቢያንስ ዲፕሎማ ያለውና በአግሪቢዝነስ፣በአግሮ ኢኮኖሚክስ ወይም በማህበራዊ ሳይንስ የትምህርት መስኮች በማርኬቲንግ፣በቢዝነስ ማኔጅመንት እና በኢኪኖሚክስ የትምህርት ዘርፍ የሰለጠነ መሆን አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ላይ ተጨማሪ ሥልጠናዎችን ያገኘ ቢሆን ይመረጣል፡፡
4. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወይም አግባብነት ያለው የክልል፤የዞን እና የወረዳ አካል በሚመድበው ቦታ ለመስራት ፈቃደኛ መሆን አለበት፣

### ለ/ የጥራት ቁጥጥር ባለሙያ

1. ስለ ጥራጥሬ ምርቶች ግብይት በቂ ዕውቀት ያለውና በመልካም ስነምግባሩ የተመሰከረለት መሆን አለበት፤
2. ቢያንስ ዲፕሎማ ያለውና በተፈጥሮ ሳይንስ የትምህርት መስኮች የሰለጠነ ሆኖ በዕፅዋት ሳይንስ፣ በጠቅላላ እርሻ፣ በአግሮኖሚ፣ በአግሪቢዝነስ እና በአግሮ ኢኮኖሚክስ ሆኖ በሙያዉ ተጨማሪ የስራ ልምድ ያለዉ መሆን አለበት ፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በጥራጥሬ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ላይ ተጨማሪ ሥልጠናዎችን ያገኘ ቢሆን ይመረጣል፡፡
4. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወይም አግባብነት ያለው የክልል፤የዞን እና የወረዳ አካል በሚመድበው ቦታ ለመስራት ፈቃደኛ መሆን አለበት፣

## 18 የጥራጥሬ ምርቶች ግብይትና ጥራት ቁጥጥር ባለሙያዎች ተግባርና ኃላፊነት

### 18.1 የፌዴራል የጥራጥሬ ምርቶች ግብይትና ጥራት ቁጥጥር ባለሙያ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ/ አዲስ ፈቃድ አውጥተው በጥራጥሬ ምርት ላኪነት የሚሰማሩ ድርጅቶችን ብቃት በየጊዜው በመገምገም የግብይትና የምርት ጥራት አጠባበቅ አቅማቸው እንዲጎለብት ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

ለ/ ላኪ ድርጅቶች በጥራጥሬ ምርት ግብይት ደንብ እና መመሪያ ላይ በተፈቀዱ አሰራሮች መሠረት እና ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ እና ከሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን ብቻ ምርት እንዲገዙ ያስገነዝባል፤ አፈፃጸሙንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ሐ/ ላኪ ድርጅቶች ከኢትዩጵያ ምርት ገበያ እና ከሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን የገዟቸውን የጥራጥሬ ምርቶች በተፈቀደላቸው የማዘጋጃ ኢንዱስትሪ እና የማከማቻ መጋዘን ብቻ ማዘጋጀታቸውንና ማከማቸታቸውን ይቆጣጠራል፣ ያረጋግጣል፣

መ/ ላኪ ድርጅቶች ወደ ውጪ በሚልኩት የጥራጥሬ ምርት ከረጢት ላይ የምርቱን ዓይነት፣ መጠን፤ የጥራት ደረጃ፤ የላኪ ድርጅቱን ስም፣ በኢትዮጵያ የተመረተ መሆኑን እንዲሁም የሚሄድበትን አገር እና የገዢ ኩባንያውን ስም የሚገልጽ ጽሁፍ የታተመበት መሆኑን ያረጋግጣል፣

ሠ/ የጥራጥሬ ምርት ላኪዎች እና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በሚኒስቴሩ የተመዘገበ ደረጃውን የጠበቀ የምርት ማከማቻ መጋዘን፣ የምርት ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ፣ በህግ ሥልጣን በተሰጠዉ አካ ል በዘመኑ የተመሰከረለት ሚዛን፣ የጥራትና የእርጥበት መለኪያ መሳሪያ፣ ከኬሚካልና ከማንኛ ውም ባዕድ ነገር የጸዳ ለጥራጥሬ ምርት መያዣነት ብቻ የሚያገለግል ከረጢት ያላቸው መሆኑን ይቆጣጠራል፣ ያረጋግጣል፤

ረ/

ላኪ ድርጅቶች ከኢትዩጵያ ምርት ገበያ እና ከሁለተኛ ደረጃ እርከን ግብይት ማዕከላት የገዟቸ ውን የጥራጥሬ ምርቶች ከባዕድ ነገሮች እንደ ነዳጅ፣ ቅባት፣ ኬሚካሎች፣ ቆዳና ሌጦ ከመሳሰሉት ጥራትን ከሚያጓድሉ ነገሮች ጋር ያለማከማቸታቸውን ወይም ያለማጓጓዛቸውን ይቆጣጠራል፣ ያረጋግጣል፤

ሰ/ ላኪ ድርጅቶች ከኢትዩጵያ ምርት ገበያ እና ከሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን የገዙትን፣ ወደ ውጭ የላኩትን እና በመጋዝናቸው የቀራቸውን የጥራጥሬ ምርት ክምችት በየጊዜው ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ሸ/ ከክልል እና ከከተማ አስተዳደር ባለሙያዎች ጋር በቅንጅት በመሆን ጥራቱን የጠበቀ የጥራጥሬ ምርት እንዲቀርብ ይሰራል ፣ ያስተባብራል ፣

## 18.2 የክልል የጥራጥሬ ምርቶች ግብይትና ጥራት ቁጥጥር ባለሙያ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ/ አምራቹ ወደ መጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት እና ወደ ሁለተኛ ደረጃ እርከን ግብይት ማዕከላት የሚያቀርባቸውን እና አቅራቢ ነጋዴዎች፣ ኅ/ሥ/ማህበራት እና አልሚ ባለሃብቶች ወደ ኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች የመጋዝን አገልግሎት ድርጅት የሚሸኟቸውን የጥራጥሬ ምርቶች በዓይነት፣ በዝርያ እና በምርት ዘመን ይቀላቀሉ በአግባቡ መዘጋጀታቸውን እና ከተረፈ ምርት፣ከባዕድ ነገሮች እና ከተባይ ነጻ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

ለ/ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት እና ወደ ሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን የሚቀርቡ የጥራጥሬ ምርቶችን የእርጥበት መጠን ትክክለኛነት ያረጋግጣል፤

ሐ/ በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት እና በሁለኛ ደረጃ የግብይት እርከን ውስጥ ሥርዓቱን የተከተለና የተስተካከለ የግብይት ሂደት መኖሩን ይቆጣጠራል፣ ያረጋግጣል፤

መ/ ጥራጥሬ አምራች አካባቢዎች የሚገኙ የምርት ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች ጥራቱን የጠበቀ ምርት ማዘጋጀታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ሠ/ በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት እና በሁለኛ ደረጃ የግብይት እርከን የተስተካከለ የግብይት ስርዓት መሰፈኑን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

ረ/ የጥራጥሬ ምርት ሲጓጓዝ አስፈላጊ መረጃ ያለስርዝ ድልዝ እና እዉነተኛ መረጃ በመሙላት ዲስፓቹ ላይ በየደረጃዉ ባሉ የክልሉ ንግድ ሴክተር መ/ቤት ህጋዊ መህተም በማድረግ መሸኘት፣

ሰ/ የግብይት ተዋናዎች በጥራጥሬ ምርት ግብይት ደንብ እና መመሪያ ላይ በተፈቀዱ አሰራሮች መሠረት ከመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት እና ከሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን ምርት እንዲገዙ ያስገነዝባል፤ አፈፃጸሙንም ይከታተላል፣

ሸ/ በጥራጥሬ ምርት ግብይት ላይ የተሰማሩ አካላትን ወይም ድርጅቶችን ብቃት በየጊዜው በመገምገም የግብይትና የምርት ጥራት አጠባበቅ አቅማቸው እንዲጎለብት ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

ቀ/ የጥራጥሬ ምርቶች መያዣ ከረጢቶችን ባዕድ ከሆኑ ነገሮች እንደ ነዳጅ፣ ቅባት፣ ኬሚካሎች፣
ቆዳ እና ጥራትን ከሚያጓድሉ ነገሮች ጋር ማከማቸት ወይም መጓጓዝ እንደሌለበት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

በ/ የጥራጥሬ ምርቶች ግዥና ሽያጭ አይነት እና መጠን፣የዋጋ ዝርዝር እንዲሁም ለግብይት ስርዓት ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች በመያዝ ፣በማደራጀት እና በመተንተን ጥቅም ላይ እንዲዉል ያደርጋል፣

ተ/ ጥራጥሬ ምርቶች መቅረብ በሚገባዉ የጊዜ ገደብ ብቻ ለኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች የመጋዘን አገልግሎት ድርጅት የማቅረብ እና ምርትን አላግባብ በመጋዘን እንዳይከማች የማስገንዘብ፣ የመከታተል ኃላፊነት አለባቸዉ፡፡

## ክፍል ስምንት

## 19. በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና በክልሎች መካከል ስለሚኖር ግንኙነት

19.1 የክልል ቢሮዎች በክልሉ ከሚገኙ የጥራጥሬ አምራች ዞኖችና ወረዳዎች ወደ መጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት የቀረበውንና ወደ ኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች የመጋዘን አገልግሎት ድርጅት የተሸኘውን የጥራጥሬ ምርቶች ዓይነት፣ መጠን እና በማን እንደተሸኘ የሚገልፅ መረጃ በማደራጀት በየወሩ እንደሁም እንደ አስፈላጊነቱ በተጠየቀ ጊዜ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያስተላልፋሉ፤

19.2 ለጥራጥሬ ምርቶች አቅርቦትና ግብይት መሻሻል ይጠቅማል ተብሎ የሚታመንበትን ማንኛውንም ጥናት ለማካሄድ የሚረዱ መረጃዎችን በማሰባሰብና አደራጅቶ በማቅረብ እንዲሁም በጥናቱ ላይ በመሳተፍ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር በቅንጅት ይሰራሉ፤

19.3 በጥራጥሬ ምርቶች አቅርቦትና ግብይት እንዲሁም በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ በሚያጋጥሙ ችግሮች ላይ በመወያየት የጋራ የመፍትሄ አቅጣጫ ማስቀመጥ የሚያስችሉ

የጋራ መድረኮችን እና ሌሎች የአሰራር ሁኔታዎችን ለማሻሻል የሚረዱ አውደ ጥናቶችን፣ ሥልጠናዎችን እና የመሳሰሉትን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር በጋራ ያዘጋጃሉ፤

19.4 የግብይት ሥርዓቱን ውጤታማነት ለማረጋገጥና የጥራጥሬ ምርቶች አቅርቦትና ግብይትን ለማሻሻል ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ ክልል ከሚንቀሳቀስ የመስክ ክትትልና ድጋፍ ቡድን ጋር በመሆን በዋና ዋና የክልሉ የጥራጥሬ አምራች አካባቢዎች የተቀናጀ የመስክ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋሉ፤

## 20. የመመሪያው ተፈጻሚነት

ይህ መመሪያ በሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ አግባብነት ባለው የክልል አካል፣ በጥራጥሬ አምራች አርሶ አደሮች፣ አልሚ ባለሃብቶች፣ አቅራቢ ነጋዴዎች፣ ኅ/ሥ/ማህበራት፣ ጅምላ ነጋዴዎች፣ ቸርቻሪዎች፣ አቀነባባሪዎች፣ ላኪዎች፣ ሸማቾች፣ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ከጥራጥሬ ምርቶች አቅርቦትና ግብይት ጋር ግንኙነት ባላቸው አካላት ላይ ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 21. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከጥቅምት 04/ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ያዕቆብ ያላ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የንግድ ሚኒስትር

## <u>በጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ተዋናዩች መካከል የሚፈፀም የኮንትራክት ሽያጭ ውል</u>

1. የጥራጥሬ ሻጭ /ድርጅት ስም---------------------------------------------------------------------------

   አድራሻ ክልል -----------------------------ዞን --------ወረዳ -----------ቀበሌ-------የቤት ቁጥር-----

   ስልክ ቁጥር-------------------------

2. የምርት ገዥ ድርጅት /ባለቤት ስም--------------------------------------------------------------------

   አድራሻ ክልል ------------------------------ዞን ----------------------ወረዳ----------------------ቀበሌ--

የቤት ቁጥር------------------ሰልክ ቁጥር -------------------------------------

3. የጥራጥሬ ምርት አይነት----------------መጠን--------------------------------- የኩንታል ------------
-
4. የጥራጥሬ ምርት ዋጋ በኩንታል--------------/--------------------- ብር ጠቅላለ ዋጋ------------
----/------------ብር
5. የኮንትራት ዉል ቁጥር-----------------የኮንትራት ዉል የሚፈጸምበት ቀን-------------ወር--------
----ዓ.ም----------
6. የጥራጥሬ ምርት ምርቱ የሚቀርብበት ጊዜ ቀን--------------------ወር-------------ዓ.ም--------------
---
7. የጥራጥሬ ምርቱ የሚቀርብበት ቦታ------------------------------------------------------------መጋዘን
8. ክፍያ የሚፈጸምበት ጊዜቀን--------------ወር---------------------ዓ.ም------------------------------

የምርቱ ዋጋ በምርቱ የጥራት ደረጃ መሰረት በማደረግ በስምምነት የሚወሰን ይሆናል ለኮንትራት ዉል ህጋዊነት የሁለቱም ተዋዋይ የሻጭና ግዢ ደርጅቶች ማህተም በዉሉ ሰነድ ላይ እንዲያርፍ ይደረጋል፡፡